በታሳቁ ዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ የመኖሪያ ቤት አድልዎ አጋጥሞኛና ብለው ይጠረጥራሉ?

## ERC በሚከተሉት ሊረዳዎ ይችላል:

**የሲቪል መብቶች ምርመራ በማድረግ:** የሰለጡኑ የሲቪል መብቶች መርማሪዎች አድልዎ እየተፈጸመ ስለመሆኑና እንዴት እንደሚፈጸም ለማወቅ ተከራዮች ወይም ገዝዎች መስለው ሊቀርቡ ይችላሉ።

የመኖሪያ ቤት አድልዎ አቤቱታ ለHUD ወይም የግዛት/የአካባቢ ድርጅቶች በማስመዝገብ ላይ በመርዳት።

**የአሳማኝ አገልግሎቶችና ማስተካከያ ጥያቄዎች ማስገባት:** የአሳማኝ አገልግሎት ወይም ማስተካከያ ጥያቄዎችን ረቂቅ በማዘጋጀት እና/ወይም አካል ጉዳተኛ ግለሰቦችን ወክሎ ለመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች በማስገባት ላይ በመርዳት።

ለሌሎች የአካባቢ የድጋፍ ምንጮች ሪፈራሎች በመስጠት።

የመኖሪያ ቤት አድልዎ ተፈጽሞብኛል ብለው የሚያምኑ ከሆነ, በስልክ ቁጥር (202) 234-3062 ለደውሉልን ወይም በ fairhousing@equalrightscenter.org ኢሜይል መላክ ይችላሉ።

ሁሉም አገልግሎቶቻችን በነጻና በሚስጥር ይቀርባሉ።

Equal Rights Center
est. 1983
Advancing Civil Rights For Over a Quarter Century

የዕኩል መብቶች ማዕከል (ERC) በመኖሪያ ቤት፣ የስራ ቅጥር፣ እና በዋሽንግተን ዲሲ እና ሀገር አቀፍ ደረጃ በማህበረሰብ የህዝብ አገልግሎቶች ላይ የሚፈጸም ህገወጥና ኢ-ፍትሀዊ አድልዎን ለይቶ ላስቀረት የሚሰራ የሲቪል መብቶች ድርጅት ነው።


የዕኩል መብቶች ማማከል
820 First St. NE, Suite LL160
Washington, D.C. 20002

ዋና ስልክ - **202.234.3062**
ነጻ ስልክ - **866.549.0009**
ሪሌይ - **711**

**www.equalrightscenter.org**
**fairhousing@equalrightscenter.org**



*©የዕኩል መብቶች ማዕከል 2016*
*መብቱ በህግ የተከበረ ነው።*



ለዚህ ህትመት መነሻ የሰጠው ስራ በዩኤስ የመኖሪያ ቤትና የከተማ ልማት መምሪያ የገንዘብ ድጋፍ ተደርጎለታል። የስራው ፍሬ ነገሮችና ግኝቶች ለህዝብ ቀርበዋል። ፀሀፊውና አታሚው በዚህ ህትመት ስር ለተካተቱ አገላለጾችና ትርጓሜዎች ትክክለኛነት ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ። እነዚህ ትርጓሜዎች የግድ የፌደራል መንግስቱን አቋሞች ማንፀባረቅ አይጠበቅባቸውም።.




# የመኖሪያ ቤት **አድልዎ** አጋጥሞዎታል?


Equal Rights Center
est. 1983
Advancing Civil Rights For Over a Quarter Century

# በአካባቢ ጥበቃ የሚደረግላቸው ምድቦች

የፍትሀዊ የመኖሪያ ቤቶች ሕግ እና የብዙ ግዛትና አካባቢ ሕጎች ጥበቃ የሚደረግለት ምድብ አባል በመሆንዎ መነሻነት የመኖሪያ ቤት አድልዎ እንዳይፈጸምብዎት ይከለክላሉ። የፌደራል የፍትሀዊ መኖሪያ ቤት ሕግ ዘርን፣ ቀለምን፣ ሀይማኖትን፣ ብሄራዊ ማንነትን፣ ጾታን፣ አካል ጉዳተኝነትን እና የቤተሰብ ደረጃን መነሻ በማድረግ ከሚፈጸም የመኖሪያ ቤት አድልዎ ጥበቃ ያደርጋል። ሜሪላንድ ውስጥ ለጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታዊ መገለጫ እና የጾታ ማንነት የሚደረጉ ተጨማሪ ግዛት አቀፍ ጥበቃዎች አሉ። ቨርጂንያ ውስጥ ለአረጋውያን (55+) ጥበቃ ይደረጋል።

## በአካባቢ ጥበቃ የሚደረግላቸው ምድቦች

- ዘር, ቀለም, ሀይማኖት, መነሻ አገር, ጾታ, አካል ጉዳት, የጋብቻ ሁኔታ, ዕድሜ, የግል ገጽታ, ጾታዊ መገለጫ, የጾታ ማንነት ወይም መገለጫ, የቤተሰብ ኃላፊነቶች, የፖለቲካ ግንኙነት, የትምህርት ደረጃ, የቤተሰብ ሁኔታ, የገቢ ምንጭ, የመኖሪያ ወይም የስራ ቦታ, የቤተሰብ ተሸጋሪ ጥቃት ተጎጂ መሆን
- ጾታዊ መገለጫ, የቤተሰብ ሀረግ, የጋብቻ ሁኔታ, ዕድሜ
- የቤተሰብ ሀረግና አዩነ ስውርነት
- የጋብቻ ሁኔታ
- የጋብቻ ሁኔታና ጾታዊ መገለጫ
- ዕድሜ, የቤተሰብ ሀረግ, የቤተሰብ ኃላፊነቶች, የጾታ ማንነት, የልጆች መኖር, የገቢ ምንጭ, የጋብቻ ሁኔታ, ጾታዊ መገለጫ, የጾታ ማንነት
- ዕድሜ, የቤተሰብ ሀረግ, የልጆች መኖር, ጾታዊ መገለጫ
- ዕድሜ, የጋብቻ ሁኔታ, ጾታዊ መገለጫ, የጾታ ማንነት, የገቢ ምንጭ
- ዕድሜ, የጋብቻ ሁኔታ, የገቢ ምንጭ
- ዕድሜ, ስራ, የፖለቲካ አስተያየት, የግል ገጽታ, ጾታዊ መገለጫ
- ዕድሜና የጋብቻ ሁኔታ




የመኖሪያ ቤት አድልዎ በአብዛኛው ድብቅና ለማወቅ አስቸጋሪ ነው።

## እዚህ ላይ ጥቂት ማስታወሻዎች/ሰንደቅ አላማዎች ቀርበዋል፡

- የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ለአጋዥ እንስሳ ክፍያ ያስከፍሉዎታል፣ ወይም እንስሳው ልዩ ስልጠና እንደወሰደ የሚያሳዩ የማስረጃ አይነት ሊጠይቅዎ ይችላል።
- የወኪል ህጻናት ስላሉት ቤተሰብ ተስፋ አስቆራጭ አስተያየቶችን መስጠት ወይም በህጻናት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ልዩ ህጎችን ማሳየት።
- ያልተያዘ ቤት ለማየት ቀጠሮ አስይዘው ሲመጡ ወኪሉ መኖሪያ ቤቱ እንደተያዘ ከነገርዎት።
- የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ሌላ ቦታ ለመኖር ቢመርጡ የተሻለ እንደሆነ እንደሚያስብ ከነገርዎ ወይም የጠየቋቸውን ሌሎች አሳማኝ አማራጮች ከከለከሉዎ።
- በገንዘብ አቅም ብቁ ቢሆኑም እንኳ ለአፓርታማ ወይም የመኖሪያ ቤት ብድር እንዳያመለክቱ ከተደረጉ።
- የመኖሪያ ቤት አቅራቢ የመኖሪያ ቤት ፋክቱሮች እንደማይቀበል፣ ወይም እንደ የገቢ መስፈርቶች የመሳሰሉ የትኛውንም የፋክቱር ያዥ ነዋሪ እዚህ (በዋሽንግተን ዲሲ እና ሞንትጎመሪ፣ የሜሪላንድ ፍሬደሪክና ሀዋርድ ካውንቲዎች) እንዳይኖር የሚገድቡ ፖሊሲዎች እንዳሉት ከነገረዎ።
- የመኖሪያ ቤት አቅራቢ የእርስዎን/የሌሎችን ጥበቃ የሚደረግለት ምድብ አባልነት መነሻ በማድረግ ስለ እርስዎ፣ ጎረቤቶችዎ ወይም እርስዎ አብረዋቸው መኖር ስለሚፈልጓቸው የመኖሪያ መንደርዎ ነዋሪዎች የተመለከቱ አጸያፊ አስተያየቶች መስጠት።

ከእነዚህ መካከል የትኛውም ካጋጠምዎ ገጠመኝዎን ወዲያውኑ ለERC ሪፖርት ስለማድረግ ያስቡ።

www.equalrightscenter.org

የመኖሪያ ቤት አድልዎ ስለመፈጸሙ ከማወቂያ አጅግ ውጤታማ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሲቢል መብቶች ምርመራ ወይም መኖሪያ ቤት በድብቅ መግዛት ነው። ERC መሪ የሲቢል መብቶች መርማሪ ሙያተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ የመኖሪያ ቤት አድልዎ ተፈጽሞብኛል ብለው ካሰቡ ምርመራ በማካሄድ ሊረዳዎ ይችላል።

ቴስተር 1




ቴስተር 2

